ቁጥር ጤበበመ/27/1756

ቀን 19/10/2009

ለአብክመ ቴክኒክ፣ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ

ለአብክመ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ

ለአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም

ባህር ዳር

ጉዳዩ፡- የሳኒቴሽን ማርኬቲንግ የመግባቢያ ሰነድ ስለመላክ

እንደሚታወቀው ሁሉ የአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ይጋለጥ የነበረውን ህብረተሰብ ግንዛቤውን በማሳደግ የሳኒቴሽን ግብዓቶችን በማቅረብ እንዲጠቀም ለማድረግ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀርጾ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አጋር ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ስራ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡

ህብረተሰቡ እየተገበረ ያለውን የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ሂደት ውጤታማ ለማድረግ የሳኒቴሽን ማርኬቲንግ ስትራቴጂ ተነድፎ በዘላቂነት መተግበር ተጀምሯል፡፡ ፕሮግራሙ በባህሪው የተለያዩ ሴክተር መስሪያቤቶችን ማሳተፍ የሚጠይቅ በመሆኑ፤

- የአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ፣
- የአብክመ ቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞችልማት ቢሮ፤
- የአብክመ ሴቶችና ህጻናት ቢሮና
- የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም በመቀናጀት ዘላቂነት ያለው የሳኒቴሽን ቁሳቁሶች ለማህበረሰቡ በማቅረብ ፕሮግራሙን ውጤታማ ለማድረግ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመናል፡፡

አራቱም የሚመለከተን ሴክተር መ/ቤቶች የተፈራረምነበትን የመግባቢያ ሰነድ አንድ ጥራዝ በዚህ ሸኝ ደብዳቤ አባሪነት መላካችንን እየገለጽን የተፈራረምን ሴክተር መ/ቤቶች የድርሻችንን እንድንወጣና ሌሎች አጋር አካላትም በዚህ ስምምነት ተገዥ ሆነው ድጋፋቸውን እንዲቀጥሉ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር!

አበበው ገበየሁ ወርቁ (ዶ/ር)
የጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ

- ለፕሮግራሞች ዘርፍ ም/ቢሮ ኃላፊ
- ለጤ/ማበ/በሽ/መከ/ዋና/ስ/ሂደት
- ለጤና/ኢክ/ኃ/አካ/ጤና/አጠ/ኬዝ ቲም
  ጤ/ጥበቃ ቢሮ

# የሳኒቴሽን ግብይትን አስመልክቶ

# በአብክ ጤና ጥበቃ ቢሮ፣ ቴ/ሙ/ኢ/ል/ቢሮ፣

# የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ እና አማራ ብድርና

# ቁጠባ ተቋም መካከል የተፈፀመ የጋራ

# የመግባቢያ ሰነድ

የካቲት 5/ 2009 ዓ.ም

ዳንግላ

ርዕስ ገፅ


መግለጫ ........ 3
1. መግቢያ ........ 4
2. የመግባቢያ ሰነዱ አላማ ........ 5
3. የመግባቢያ ሰነዱ ግብ ........ 5
4. በቅንጂት መስራት ያስፈለገበት ምክንያት ........ 6
5. ስምምነቱ የሚተገበርባቸው ወረዳዎች ........ 6
6. የሚመለከታቸው ስምምነት ፈጻሚ መ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ........ 6
6.1 የጤና ጥበቃ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት ........ 6
6.2 ቴ/ሙ/ኢ/ል ቢሮ ........ 7
6.3 ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ........ 8
6.4 አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ........ 8
7. የስምምነቱ የግምገማ ስርዓት ........ 9
8. ስምምነቱ የሚጸናበትና የሚያበቃበት ጊዜ ........ 9
9. ስምምነቱ የሚከለስበት ሁኔታ ........ 9
10. የተፈራራሚ ባለድርሻ አካላት ፊርማና ማህተም ........ 9

## መግለጫ

ይህ የመግባቢያ ሰነድ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ፣ ቴ/ሙ/ኢ/ል ቢሮ፣አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም እና ሴቶችና ህጻንት ጉዳይ ቢሮ መካከል የሳኒቴሽን ግብይት ስራን ለማጠናከርንና ማህበረሰቡን የተሻሻለ የሳኒቴሽን ጠቀሜታ ላይ ለማዋል የሚተገበሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የአመለካከት ለውጥ፣ በግንባታ ሙያ ያላቸውን ኢንተርፐራይዞች በማሰባሰብ የተጠቃሚዎች ፍላጎት በጋራ ለመስራት ታሳቢ ያደረገ መግባቢያ ሰነድ ነው፡፡

"ጤና ጥበቃ ቢሮው" ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለውን የሳኒቴሽን ግብይት በተመረጡ የክልሉ ወረዳዎች ለሚኖሩ አርሶ አደሮች ለማስራጨት ፍላጎት የማሰባሰብ፣ ቴክኖሎጂዎቹ በሚፈለገው ጥራት መሆናቸውን የመከታተል፣የተፈጠረውን አደረጃጀት በመጠቀም የመቀስቀስ ፣ በቴክኖሎጂው ጠቅላላ ጠቀሜታና አጠቃቀም ዙሪያ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ የማስጨበጥና የመከታተል ስራዎችን ያከናውናል፡፡

"ቴ/ሙ/ኢ/ልማት ቢሮ" ብዙ ጠቀሜታ ያለውን የሳኒቴሽን ግብይት ስራ ነባር የተደራጁ ወጣቶችን በማጠናከር ወይም አዲስ በማደራጀት የንግድና የማምረት ክህሎት ስልጠና በመስጠት ህጋዊነትን በማስያዝ የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ እንዲፈፀሙ ድጋፍ ክትትል ያደርጋል፡፡

"ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮው" የእናቶችና ህጻናት ሞትን በመቀነስ ጠቀሜታ ያለውን የሳኒቴሽን ግብይት በተመረጡ የክልሉ ወረዳዎች ለሚኖሩ አርሶ አደሮች ለማስራጨት ማህበረሰቡ ፍላጎት እንዲኖረው ለማደረግ የተፈጠረውን አደረጃጀት በመጠቀም የቅስቀሳ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

"አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም" ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለውን የሳኒቴሽን ግብይት በተመረጡ የክልሉ ወረዳዎች ለሚኖሩ አርሶ አደሮች ለማስራጨት እንዲቻል ለነባር ወይም አዲስ ለሚደራጁ ወጣቶች ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ብድር ማመቻቸትና መከታተል ስራውን ያከናውናል፡፡

በመሆኑም ተቋማቶቹ ከታች በተዘረዘሩት ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ስራዎችን በጋራ ለማከናወን ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡

## 2. በቅንጅት መስራት ያስፈለገበት ምክንያት

እንደሚታወቀው የሳኒቴሽን ግብይት የበርካታ ሴክተር መ/ቤቶችን ስራ አስተሳስሮ የያዘ በመሆኑ የነዚህን መ/ቤቶች የጋራ ጥረትና ትግበራ ይጠይቃል። በመሆኑም ቴክኖሎጂው ለአርሶ አደሩ ከሚሰጠው ትርጉም ያለው ጠቀሜታ፣ ተቋማቶቹ በግንዛቤ ማስጨበጫ፣ በአመለካከት ለውጥ፣ በግንባታና በሥራ ዕድል ፈጠራ ተቀናጅተው መስራታቸው ቴክኖሎጂው ይበልጥ እንዲስፋፋ፣ የሴቶችና ህጻናት ጤንነት እንዲሻሻል እና የስራ እድል ፈጠራን በመጨመር ሁለንተናዊ እድገትን ይጨምራል።

## 3. ስምምነቱ የሚተገበርባቸው ወረዳዎች

ቅንጅታዊ ስራው ውጤታማ እንዲሆን በተወሰኑ ፓይለት ወረዳዎች በመጀመር በተግባር አፈጻጸም የታዩ ችግሮችን እየገመገሙ እያረሙ በስፋት ለመሄድ እንዲያስችል፡-

- በምስራቅ ጎጃም ዞን ፡- ደባይ ጥላትግንና ማቻከል ወረዳዎች
- በምራብ ጎጃም ዞን፤- ሜጫና ሰከላ ወረዳዎች
- ሰሜን ጎንደር ዞን ፤- ደንቢያና ዳባት ወረዳዎች
- በአዊ ዞን፡- ዳንግላ ዙሪያ ወረዳ
- ደ/ጎንደር ዞን፡- እስቴ ወረዳ
- ሰ/ሸዋ ዞን ፡- ሞረትናጅሩና ቀወት ወረዳዎች
- ሰ/ወሎ ዞን፡- መቄት ወረዳ
- ደ/ወሎ ዞን፡- ተሁለደሬና ለጋንቦ ወረዳዎች

በድምሩ 13 ወረዳዎች ላይ የቅንጅት ስራው እዲጀመር የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡

## 4. የሚመለከታቸው ስምምነት ፈጻሚ መ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

### 4.1 የጤና ጥበቃ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- ፕሮግራሙን የመምራት፣ የማስተባበርና የማስፈጸም፤
- በክልል ደረጃ ስለፕሮግራሙ እውቅና እንዲኖር ወረክ ሾፕ ማዘጋጀት
- የማህበረሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ዲዛይኖችን ማቅረብ
- ቴክኖሎጂው በጥራት እንዲመረት ክትትል ማደረግ

## 2. በቅንጅት መስራት ያስፈለገበት ምክንያት

እንደሚታወቀው የሳኒቴሽን ግብይት የበርካታ ሴክተር መ/ቤቶችን ስራ አስተሳሰር የያዘ በመሆኑ የነዚህን መ/ቤቶች የጋራ ጥረትና ትግበራ ይጠይቃል። በመሆኑም ቴክኖሎጂው ለአርሶ አደሩ ከሚሰጠው ትርጉም ያለው ጠቀሜታ፣ ተቋማቶቹ በግንዛቤ ማስጨበጫ፣ በአመለካከት ለውጥ፣ በግንባታና በሥራ ዕድል ፈጠራ ተቀናጅተው መስራታቸው ቴክኖሎጂው ይበልጥ እንዲስፋፋ፣ የሴቶችና ህጻናት ጤንነት እንዲሻሻል እና የስራ እድል ፈጠራን በመጨመር ሁለንተናዊ እድገትን ይጨምራል።

## 3. ስምምነቱ የሚተገበርባቸው ወረዳዎች

ቅንጅታዊ ስራው ውጤታማ እንዲሆን በተወሰኑ ፓይለት ወረዳዎች በመጀመር በተግባር አፈጻጸም የታዩ ችግሮችን እየገመገሙ እያረሙ በስፋት ለመሄድ እንዲያስችል፡-

- በምስራቅ ጎጃም ዞን ፡- ደባይ ጥላትግንና ማቻክል ወረዳዎች
- በምራብ ጎጃም ዞን፤- ሜጫና ስከላ ወረዳዎች
- ሰሜን ጎንደር ዞን ፤- ደንቢያና ዳባት ወረዳዎች
- በአዊ ዞን፡- ዳንግላ ዙሪያ ወረዳ
- ደ/ጎንደር ዞን፡- እስቴ ወረዳ
- ሰ/ሸዋ ዞን ፡- ሞረትናጅሩና ቀወት ወረዳዎች
- ሰ/ወሎ ዞን፡- መቄት ወረዳ
- ደ/ወሎ ዞን፡- ተሁለደሬና ሊጋንቦ ወረዳዎች

በድምሩ 13 ወረዳዎች ላይ የቅንጅት ስራው እዲጀመር የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡

## 4. የሚመለከታቸው ስምምነት ፈጻሚ መ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

### 4.1 የጤና ጥበቃ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- ፕሮግራሙን የመምራት፣ የማስተባበርና የማስፈጸም፤
- በክልል ደረጃ ስለፕሮግራሙ እውቅና እንዲኖር ወረክ ሾፕ ማዘጋጀት
- የማህበረሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ዲዛይኖችን ማቅረብ
- ቴክኖሎጂው በጥራት እንዲመረት ክትትል ማደረግ

- በተመረጡ ፓይለት ወረዳዎች የወረዳ የጤና ባለሙያዎች፣ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙዎችና የጤና የልማት ሰራዊት በቴክኖሎጂው ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ
- አደረጃጀቱን በመጠቀም የህብረተሰቡን ፍላጎት ዳሰሳ ማካሄድና መመዝገብ
- አደረጃጀቱን በመጠቀም ለማህበረሰቡ የሳኒቴሽን ግብአቶችን የማስተዋወቅና የገቢያ ትስስሩን ማጠናከር
- የፕሮግራሙን አፈጻጸም መደገፍ፣መከታተልና መገምገም
- አጋር አካላትን በማስተባበር ለፕሮግራሙ መሳካት እንዲሳተፉ መጋበዝና መከታተል፡፡

## 4.2 ቴ/ሙ/ኢ/ል ቢሮ

- የቢሮውን አደረጃጀት ተከትሎ በዞን መምሪያዎችና በወረዳ ያሉ ጽ/ቤቶች ሥራውን በባለቤትነት ይዘዉ ድጋፍንና ክትትል እንዲደረጉ፣የግንዛቤ ስራ እንዲሰሩ ማድረግ
- ስልጠናዉን የሚሰጡ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችን መለየት
- ስልጠናዉን የሚሰጡ አስልጣኞችን በመለየት የአሰልጣኞች ስልጠና/ቲኦቲ/ ስልጠና መስጠት
- ስልጠናዉን መስጠት የሚያስችል የሙያ ደረጃዉንና ስርዓተ ትመህረቱን መሠረት ያደረገ TTLM ማዘጋጀት
- በአዲስ ኢንተር ፕራይዞችን በማደራጀት የንግድ ክህሎት ፣የቴክኒክ ስልጠና የንግድ ስራ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግ በመጨረሻ ብቃተቸዉ በምዘና እንዲረጋገጥ ማድረግ
- የመመስረቻ ጽሁፍ ፣ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም ቢዝነስ ፕላን በማዘጋጀት ሕጋዊ የሆነ ኢንተርፕራይዝ መመስረት
- የምክርና መረጃ አገልግሎት መስጠት፣
- በንግድ ዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- ኢንተርፕራይዞቹ የሚመሩበትን የበጀት አጠቃቀምና የግዥ ሥርዓት መመሪያ ያዘጋጃል፣
- ኢንተርኘራይዞቹ የራሳቸው ቁጠባ እንዲኖራቸው ድጋፍ ማድረግና ለቀጣዩ ሽግግር የመስሪያና መሸጫ ቦታ ማመቻቸት፣

- ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችን በፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጆች እንዲሰሩ የማድረግ
- የኢንድስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት መስጠትና የገባያ ትስስር መፍጠር
- የቁጥባ ባህልን ለማዳበር ቅስቀሳ ማድረግ

## 4.3 ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ

- የቢሮውን አደረጃጀት ተከትሎ በወረዳ ያሉ ጽ/ቤቶች ሥራውን በባለቤትነት ድጋፍንና ክትትል እንዲደረጉ፣የማንዛቤ ስራ እንዲሰሩ ማድረግ
- የሴቶች አደረጃጀትን መደገፍ፣ መከታተልና ማጠናከር
- አደረጃጀቱን በመጠቀም የህብረተሰቡን ፍላጎት ዳሰሳ ማካሄድና መመዝገብ
- አደረጃጀቶችን በመጠቀም ለማህበረሰቡ ቅስቀሳ በማደረግ የገበያ ትስስሩን ማጠናከር
- የቁጥባ ባህልን ለማዳበር ቀስቀሳ ማድረግ

## 4.4 አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም

- የቢሮውን አደረጃጀት ተከትሎ በወረዳ ያሉ ጽ/ቤቶች ሥራውን በባለቤትነት ድጋፍና ክትትል እንዲደረጉ፣የማንዛቤ ስራ እንዲሰሩ ማድረግ
- የሚቀርበዉን ቢዝነስ ዕቅድ በመተንተን ብድር ማዕደቅና መስጠት
- ለተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች የገንዘብ አጠቃቀማቸዉን ለማጠናከር ድጋፍና ክትትል ማደረግ
- ለተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ ድጋፍ ማደረግ
- ለብደር የሚሆን ቁጠባና ፈንድ የማሰባስብ ስራ ይሰራል።
- የቁጥባ ባህልን ለማዳበር ቀስቀሳ ማድረግ

5. የዚህ ኮሚቴ አበላት እንዳሉ ሆኖ ለስራዉ አስፈላጊ ናቸዉ የሚባሉ ሌሎች ኮሚቴዎችም ሊካተቱ ይችላሉ

6. የስምምነቱ የግምገማ ስርዓት

የስምምነቱ አፈጻጸም ከሁሉም መ/ቤቶች ተውጣጥቶ በሚቋቋመው ቴክኒካል ኮሚቴ በየወሩ አፈጻጸሙንና የታዩትን ችግሮች በመስከም ሆነ በቢሮ በመገምገም ሪፖርቱን ለቢሮአቸው ያቀርባሉ። በቢሮ ኃላፊዎች ደረጃ አፈጻጸሙ በ3 ወሩ እየተገመገመ የታዩት ችግሮች እንዲታረሙ አቅጣጫ ይቀመጥባቸዋል። የተወሰኑ ውሳኔዎችም በቃለ ጉባኤ ተይዘው በሚቀጥለው ስብሰባ እርምት መወሰድ አለመወሰዱን ይገመገማሉ።

7. ስምምነቱ የሚጸናበትና የሚያበቃበት ጊዜ

ስምምነቱ ተፈጻሚ ሚሆነው የሁሉም መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በጋራ መግባቢያ ሰነዱ ላይ ከተፈራረሙ ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል የሚጠናቀቅበት ጊዜ እንዳስፈላጊነቱ በስምምነት ሊራዘም ይችላል።

8. ስምምነቱ የሚከለስበት ሁኔታ

ይህ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በሚያደርጉት ውይይትና በሚደርሱበት አቋም መሰረት በማንኛውም ጊዜ ሊከለስ ይችላል።

9. የተፈራራሚ ባለድርሻ አካላት ፊርማና ማህተም

የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ/ተወካይ

ኃላፊ/ተወካይ

ስም፣ ----------------------------------------

ፊርማ፣ ----------------------------------------

ቀን፣ ----------------------------------------

አበባው ጋሻው ወርቁ (ዶ/ር)
የጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ

የክልሉ ቴ/ሙ/ኢ/ል ቢሮ

ስም፣ ---- በላይ ዘለቀ መንግስቱ ም/ቢሮ ኃላፊ ----

ፊርማ፣ ----------------------------------------

ቀን፣ ---- 03/08/2009 ----

**የክልሉ ሴ/ህ/ጉዳ ቢሮ ኃላፊ/ተወካይ**

ስም፡ ------------------------------

ፊርማ፡ ------------------------------

ቀን፡ 07/10/09

**አማር ብድርና ቁጠባ ተቋም ኃላፊ/ተወካይ**

ስም፡ አጋገር ጌታሁን ምክትል የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ

ፊርማ፡ ------------------------------

ቀን፡ 05/06/09

Amhara Credit and Saving Institution (S.C)